Ethiopian Community in Seattle

Washington State Department of Labor & Industries

ለቀጣሪ ተደራሽነት እና ትምህርት ከሰራተኛ እና ኢንዱስትሪዎች መምሪያ ጋር በመተባበር።

በዋሽንግተን ግዛት አነስተኛ የንግድ ሥራ መጀመር፦ ሊታወቁ የሚገባቸው ዋና ዋና የL&I መስፈርቶች

መግቢያ

በዋሽንግተን ግዛት ውስጥ የንግድ ሥራ ሲጀምሩ ወይም ሲያካሂዱ ሊወጧቸው የሚገቡ ዋና ዋና ኃላፊነቶች አሉ። የዋሽንግተን ግዛት የሥራ እና ኢንዱስትሪ መመሪያ (L&I) የንግድ ተቋማት ዋና ዋና መስፈርቶችን እንዲያከብሩ እና ሠራተኞቻቸውን እንዲጠብቁ የሚያግዙ ነፃ መርጃዎችን ያቀርባል።

እነዚህን መሠረታዊ ጉዳዮች በሚገባ መረዳትዎ ካልተፈለጉ አደጋዎች/ኪሳራዎች ለመጠበቅ እና ስኬታማ የንግድ ሥራ ለመገንባት ይረዳዎታል።

1. መለጠፍ የሚገባቸው የሥራ ቦታ ማስታወቂያዎች

አሰሪዎች ሠራተኞች በቀላሉ ሊያዩዋቸው በሚችሉባቸው ቦታዎች ላይ የL&I ይፋዊ ማስታወቂያዎችን (Posters) የመለጠፍ ግዴታ አለባቸው። እነዚህ ማስታወቂያዎች ሠራተኞችን ስለ መብቶቻቸው እና ስለ ሥራ ቦታ ጥበቃዎቻቸው መረጃ ይሰጣሉ። እነዚህን ማስታወቂያዎች ከL&I ድረ-ገጽ ላይ በነፃ ማዘዝ ይቻላል።

2. የሰነድ አያያዝ መስፈርቶች

የንግድ ተቋማት የደመወዝ ክፍያ (Payroll) እና የሠራተኞችን የግል መዝገብ ሰነዶች ቢያንስ ለሦስት ዓመታት ማቆየት ይኖርባቸዋል፤ በተጨማሪም የሠራተኞች የግል መረጃ በምስጢርና በደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ መቀመጥ ይኖርበታል።

3. በሥራ ቦታ የደህንነት ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነት

ማንኛውም የሥራ ቦታ (በሩቅ ወይም ከቤት ሆኖ መሥራትን ጨምሮ) የደህንነት ሕጎችን መከተል አለበት።

አሰሪዎች የሚከተሉትን ማድረግ ይኖርባቸዋል፦

- አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮችን (Hazards) መለየት እና ማስተካከል
- በጽሑፍ የአደጋ መከላከያ መመሪያ ማዘጋጀት
- ለሠራተኞች የደህንነት ስልጠና መስጠት
- መደበኛ የደህንነት ስብሰባዎችን ማካሄድ

4. የሠራተኞች ካሳ ኢንሹራንስ

አሰሪዎች ለሠራተኞቻቸው የሠራተኞች ካሳ ዋስትና የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፤ ይህም የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦

- ሙሉ ሰዓት እና በትርፍ ሰዓት የሚሠሩ ሠራተኞችን
- ጊዜያዊ ሠራተኞችን
- በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ነፃ ተቋራጮችን (Independent contractors)

አሰሪዎች የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው፦

- የL&I አካውንት መክፈት
- በየሦስት ወሩ የሠራተኞችን የሥራ ሰዓት ማሳወቅ
- የሚፈለገውን የኢንሹራንስ መክፈያ በወቅቱ መክፈል

5. የምንዳ (የደሞዝ) እና የሥራ ሰዓት መስፈርቶች

ማንኛውም አሰሪ የሚከተሉትን የመንግሥት ሕጎች የመከተል ግዴታ አለበት፦

- ዝቅተኛውን የምንዳ (የደሞዝ) ክፍያ
- የትርፍ ሰዓት ክፍያ (በሳምንት ከ40 ሰዓት በላይ ለሚሠራ ሥራ የ1.5 እጥፍ ክፍያ)
- የሚከፈልበት የሕመም ፈቃድ
- የእረፍት እና የምግብ ሰዓት ዕረፍቶች

6. የሠራተኞች መብት እና ጥበቃ

ማንኛውም ሠራተኛ የሚከተሉት መብቶች አሉት፡-

- ከበቀል እርምጃ የመጠበቅ መብት
- ጥበቃ በሚደረግላቸው ማህበራዊ ክፍሎች/ቡድኖች (Protected class) ውስጥ በመካተታቸው ምክንያት ሳይገለሉ፣ እኩል ክፍያ እና እኩል የሥራ ዕድል የማግኘት መብት
- ስለ የምንዳ (የደሞዝ) የመወያየት መብት
- ተገቢው ክፍያ የመከፈል እና ግልጽ የሆኑ የሥራ ማስታወቂያዎችን የማግኘት መብት

7. ከL&I የሚሰጥ ድጋፍ

L&I የንግድ ተቋማት ስኬታማ እንዲሆኑ የሚያግዙ የሚከተሉትን ነፃ አገልግሎቶች ያቀርባል፡-

- የደህንነት ምክክሮች
- የስልጠና እና የትምህርት መርጃዎች
- የንግድ ሥራ መመሪያዎች

ማጠቃለያ

የአነስተኛ የንግድ ተቋማት ባለቤቶች የL&I ዋና ዋና ሕጎችን በመረዳትና በመተግበር፣ ለሠራተኞቻቸው አስተማማኝ የሥራ አካባቢ መፍጠር ይችላሉ፤ ይህም ሠራተኞችን ከአደጋ ከመጠበቁም በላይ ንግዱ በሰላምና በስኬት እንዲቀጥል ያደርጋል።

ዋቢ መረጃዎች (References materials)

L&I – **Business Essentials**

ጠቃሚ የመረጃ ምንጮች (Resources)

ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት፡-

- ይጎብኙ፡- Lni.wa.gov
- ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት ወይም ድጋፍ ከፈለጉ፣ በሚፈልጉት ቋንቋ አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ። የአነስተኛ ንግድ ቢሮን ያነጋግሩ፡- SmallBusiness@Lni.wa.gov, ወይም በዚህ በስልክ ቁጥር ይደውሉ 1-800-987-0145.
- በL&I መሠረታዊ የስልጠና አውደ-ጥናቶች እና ማዕከል *Workshops and Training Center* ላይ መመዝገብ ይችላሉ፤ በመቀጠልም መፈለጊያ ሳጥኑ (Search field) ውስጥ “L&I Essentials for Business Webinar” ብለው በመጻፍ መፈለግ ይችላሉ።
- ይጎብኙ፡- Lni.wa.gov/BusinessEssentials
- ይጎብኙ፡- ecseattle/socialmedia ወይም በዚህ በስልክ ቁጥር ይደውሉ 206-325-0304